# በኦሮሚያ ክልል፣ በጉጂ ዞኖች ውስጥ የሚፈፀሙ ከባድ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን አስመልክቶ የሰላም፣ ፍትሕ እና ተጠያቂነት ጥሪ

ሴንተር ፎር አድቫንስመንት ኦፍ ራይትስ ኤንድ ዴሞክራሲ (የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል - ካርድ)

ሰኔ 8፣ 2016

በኦሮሚያ ክልል፣ ጉጂ ዞኖች፣ ለዓመታት የዘለቀ ነውጥ አዘል ግጭት በታጣቂዎች እና በመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች መካከል ሲካሔድ ከርሟል። በዚህም ሳቢያ አሰቃቂ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እየደረሱ ቢሆኑም ጉዳዩ የሚገባውን ያህል ትኩረት ሊያገኝ አልቻለም። ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት ካርድ፣ ባለፈው አንድ ዓመት ከመንፈቅ፣ ከተለያዩ የጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ ዞን ነዋሪዎች ጋር የምክክር መድረክ በማመቻቸት በነውጥ አዘል ግጭቶቹ ሳቢያ ንፁኃን ላይ የደረሱ ተፅዕኖዎችን ለመረዳት ሞክሯል። በመቀጠልም፣ ከአካባቢው ለተውጣጡ ምሁራን፣ የመብቶች ተሟጋቾች፣ እና ሌሎችም የሰብዓዊ መብቶችን ጥሰቶች መከታተል፣ መሰነድ እና ሪፖርት ማድረግ የሚያስችል ሥልጠናዎችን ሰጥቷል። ይሁንና እነዚህ ጥረቶችም ቢሆኑ የጉጂ ዞኖች ነዋሪዎችን ሰቆቃ ለብዙኃን ማድረስ ባለመቻላቸው፣ ከጋዜጠኞች ጋር በመተባበር 36 ማሳያ ታሪኮችን በመሰብሰብ በዛሬው ዕለት ይፋ ያደርጋል።

የሪፖርቱ ዓላማ ነውጥ አዘል ግጭቶች፣ በተለይም በጉጂ ሁለት ዞኖች የንፁኃን ሕይወት ላይ እያደረሱ ያሉትን ለመስማት የሚቸግር ተፅዕኖ እንደማሳያ በማቅረብ፣ በሌሎችም የኢትዮጵያ አካባቢዎች ያሉ ነውጥ አዘል ግጭቶች በሙሉ በተኩስ አቁም ተቋጭተው፣ በፖለቲካ ድርድር እንዲፈቱ እና ዜጎች ሰላማዊ፣ የተረጋጋ ሕይወት ማግኘት እንዲችሉ ውትወታ ለማድረግ ነው።

በሪፖርቱ የተካተቱት 36ቱ ማሳያ ታሪኮች - በአማፂ ታጣቂዎችና በመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች ከሕግ ውጪ ንፁኃን ላይ የተፈፀሙ ግድያዎች፣ የዘፈቀደ እና የጅምላ እስሮች፣ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች፣ የንብረት ውድመት፣ አስገድዶ የመሰወር እና የገንዘብ ማግኛ እገታ ድርጊቶች፣ የማሰቃየት እና ኢሰብዓዊ አያያዝ የመፈፀም፣ እንዲሁም የማፈናቀል ድርጊት የተፈፀመባቸው ንፁኃን ዜጎችን ታሪኮች የያዙ ናቸው።

በነዚህ ነውጥ አዘል ግጭቶች በዓለም ዐቀፍ፣ በአገር ዐቀፍ፣ እና ክልላዊ ሕግጋት የተከበሩ መብቶችን እና ነጻነቶችን የሚጋፉ ድርጊቶች፣ እንዲሁም አሰቃቂ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ሳቢያ ዛሬ፣ ዛሬ በጉጂ መደበኛ ሕይወት ለጊዜው ተቋርጧል።

የነውጥ አዘል ግጭቶቹ ተጠቂ የሆኑት የጉጂ ዞኖች ነዋሪዎች ሰላም ይሻሉ፣ ፍትሕ ይሻሉ፣ ከደረሰባቸው አካላዊ እና ሥነ ልቦናዊ ጉዳት ማገገም ይፈልጋሉ፣ የወደመባቸው ንብረት እንዲተካ፣ የተስተጓጎለው ሕይወታቸው እንዲቀጥል እና እንደዜግነታቸው መልሰው እንዲቋቋሙ ይሻሉ። ይገባቸዋልም!

ስለሆነም፣ ካርድ በዛሬው ዕለት ለጉጂ ነዋሪዎች ድምፅ መሆን ይፈልጋል!

በነውጥ አዘል ግጭቶች ሳቢያ ለአሰቃቂ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች የተዳረጉት፣ መሠረተ ልማት እና የግል ንብረቶቻቸው የወደሙባቸው፣ ከቀዬዎቻቸው የተፈናቀሉ፣ የተገደሉ እና ንፁኃን ወዳጅ ዘመዶቻቸውን ያጡ፣ ኢትዮጵያውያን በሁሉም ክልሎች አሉ። በትግራይ ነውጥ አዘል ግጭቶች ቢቀንሱም፣ ብዙኃን እስካሁን ፍትሕና መልሶ ማቋቋም ይጠብቃሉ፣ አብዛኛው የምዕራብ ኦሮሚያ ነዋሪዎች አሁንም በነውጥ አዘል ግጭቶች ዐውድ

ውስጥ እየኖሩ ነው። በአማራ ክልል አብዛኛዎቹ አካባቢዎች የሚኖሩ ዜጎች በአማፂ ታጣቂዎች እና በመንግሥት ኃይሎች መካከል ባሉ ውጊያዎች መሐል ተጣብቀው እየኖሩ ነው። በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልልም ሁኔታው ተመሳሳይ ነው።

በአገራችን ኢትዮጵያ ያሉት ነውጥ አዘል ግጭቶቹ ባልደረሰቡባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ዜጎችም ቢሆኑ የተፅዕኖው ሰለባ ከመሆን አልዳኑም። ጋዜጠኞች እና የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ሥራዎቻቸውን ባግባቡ መሥራት የማይችሉባቸው የፖለቲካ ምኅዳር እየተፈጠረ ነው። የኢኮኖሚ ጫናውም ከፍተኛ ሆኗል።

ስለሆነም፣ ካርድ ለሁሉም በነውጥ አዘል ግጭቶች ሳቢያ ሰላም፣ ፍትሕ እና ተጠያቂነት ለተነፈጉ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ድምፅ መሆን ይፈልጋል!

ነውጥ አዘል ግጭቶች ባሉበት ምኅዳር አሰቃቂ የሰብዓዊ መብቶች ይበረከታሉ፣ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መገንባት አይቻልም፣ የተረጋጋ ኢኮኖሚ ማኖር ይቸግራል፣ የመንግሥት ቅቡልነት እና ተጠያቂነት ያሽቆለቁላል። ካርድ በነውጥ አዘል ግጭቶች የሚመጣ አዎንታዊ ለውጥ አለ ብሎ አያምንም።

ስለሆነም፣ በነውጥ የሚሳተፉ አካላት በሙሉ በአስቸኳይ የተኩስ አቁም ላይ እንዲደርሱ፣ ለችግሮቻችን ዘላቂ መፍትሔ ለማግኘት ሐቀኛ እና አሳታፊ ድርድሮች እንዲደረጉ፣ በነውጥ አዘል ግጭቶች ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎች ፍትሕ እንዲያገኙ፣ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ፈፃሚዎች ተጠያቂ እንዲሆኑ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የበኩላችንን እንድንወጣ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

#VoiceForGuji
በጉጂ እና ሌሎችም የኢትዮጵያ ክፍሎች ነውጥ አዘል ግጭቶች ንፁኃን ዜጎች ላይ እያደረሱ ያሉትን ከፍተኛ ተፅዕኖ ግንዛቤ የሚያሳድጉ መልዕክቶችን በማስተላለፍ የሰላም፣ የፍትሕ እና ተጠያቂነት ዘመቻችንን በማኅበራዊ ሚዲያዎች ይቀላቀሉ - @CARDEthiopia

# Call for End to Violence, for Justice and Accountability on Violations and Abuses of Human Rights in Ethiopia's Guji Zones

Center for Advancement of Rights and Democracy (CARD)
June 15, 2024

For years, the Guji zones of Ethiopia's Oromia region have been marred by violent conflict between armed rebels and government security forces. This violence has resulted in horrific human rights violations against civilians, an issue that has not received adequate attention.

Over the past year, CARD has actively engaged in the Guji crisis. We facilitated consultations with residents of the Guji and West Guji zones to understand the impact of the conflict on innocent people. Additionally, CARD trained local academics and human rights activists to monitor and document these violations.

Recognizing the need to raise awareness, CARD partnered with journalists to collect and publish 36 powerful case stories in English, Amharic, and Afaan Oromoo. These stories expose the devastating consequences of the conflict, including extrajudicial killings, mass and arbitrary detention, gender-based violence, property destruction, forced disappearances and extortion, torture and inhumane treatment, and displacement.

The ongoing violence constitutes a flagrant violation of international, national, and regional laws. It has shattered any semblance of normalcy in the Guji zones. The residents yearn for peace, justice, accountability and the opportunity to rehabilitate their shattered lives.

CARD stands as a voice for the people of Guji.

However, the plight of the Guji people is not unique. Ethiopians across various regions have endured horrific human rights violations, infrastructural damage, displacement, and the loss of loved ones due to conflict. While tensions have mostly eased in Tigray, many yearn for justice, accountability and restoration. Western Oromia remains a war zone, and citizens in many parts of Amhara and Benishangul-Gumuz are caught in the crossfire.

Even those residing in seemingly peaceful areas experience the repercussions of violence. Civic space shrinks as journalists and human rights defenders struggle to operate freely. Moreover, the economic impacts of these conflicts ripple across the nation.

CARD would like to amplify the voices of all Ethiopians denied peace, justice, and accountability.

In the context of violence, human rights are trampled, democratic progress stalls, economies falter, and public trust in governance erodes. CARD also firmly believes that positive change cannot be achieved through violence means.

We urge all parties involved in the violence to commit to an immediate cessation of hostilities, genuine and inclusive negotiations and dialogue must be conducted to find lasting solutions, and those who have inflicted harm must be held accountable, and victims served justice. Only through these actions can Ethiopia heal and move towards a future of peace and stability.

#VoiceForGuji
Join us in our calls for peace, justice, and accountability through raising awareness of the impact of violent conflicts on the civilian population in Guji and elsewhere through social media campaigns @CARDEthiopia.